**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**ሰበር ሰሚችሎት**

የሰ/መ/ቁ 208834

ሚያዚያ 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- የወ/ሮ ልኬ አየለ ወራሾች

1ኛ. ወ/ሮ ሸዋዬ ለማ } ቀረቡ

2ኛ. አቶ አበራ ለማ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ካሳሁን ተስፋዬ፡- ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሪት ዘለቃሽ ጥላሁን፡- ተወካይ 1ኛ ተጠሪ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 04/10/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 168292 በቀን 17/08/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 239737 በቀን 06/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ሲሆን የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ ልኬ አየለ ተከሳሽ ነበሩ።

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች በቀን 28/07/2002 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ የከሳሾች አያት አቶ ሽፈራው ወ/ኪዳን የካቲት 11/1970 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ከመለየታቸው በፊት በህይወት እያሉ በቀድሞ አጠራር ወረዳ 04 ቀበሌ 37 በአሁኑ ልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 05/08 የቤ.ቁ 860 እና 861 የሆኑ ቤቶች በስማቸው የተመዘገቡ አፍርተዋል። አቶ ጌታቸው ሽፋራው እና ወ/ሮ አስካለ ሽፋራው የተባሉ ልጆችም ወልደዋል። ንብረቱን አጎታችን አቶ ጌታቸው እና እናታችን ወ/ሮ አስካለ ተከፋፍለው ሁለቱም በሞት ስለተለዩ የእናታችን ድርሻ የሆነውን የቤ.ቁ 861 የሆነውን ቤት ከሳሾች ይዘን የምንገኝ ሲሆን የአጎታችን ድርሻ የሆነውን ተከሳሽ አላግባብ ይዘው እያከራዩ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። በመሆኑም ጥር 06/2002 ዓ.ም በቀረበውና በመ/ቁ 123227 በቀን 27/05/2002 ዓ.ም በጸደቀው የውርስ ሪፖርት መሰረት ተከሳሽ የቤ.ቁ 860 የሆነውን ቤት እንዲያስረክቡን፤ በወር 200.00 (ሁለት መቶ) ብር ኪራይ አጎታችን ከሞተበት ከየካቲት 1989 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን እስከሚያስረክቡበት ግዜ ድረስ ያለውን ኪራይ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል።

የስር ተከሳሽ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል። ፍ/ቤቱ የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል አስቀድሞ ግንቦት 04/2006 ዓ.ም በብይን መዝገቡን ዘግቶ የነበረ ሲሆን ጉዳዩ እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመ/ቁ 116983 ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በዋለ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ተከሳሽ ከኑዛዜ ውጪ በአከራካሪው ቤት ላይ ያቋቋሙት መብት ያላቸው መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በነጥብ መልሷል። በዚህ መልኩ የተመለሰለት የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ክርክሩን ሰምቷል።

ተከሳሽ በፍሬ ነገሩ ላይ ባቀረቡት ክርክር ከሳሾች የአጎታችን ቤት በማለት የጠየቁት የቤ.ቁ 860 የባለቤቴ አቶ ጌታቸው ሽፈራው እና የእኔ የጋራ ንብረት ነው፤ ቤቱን ልለቅ አይገባም በማለት አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም ከሰበር ችሎት በተያዘው ጭብጥ መሰረት ለማጣራት የከሳሾችን ምስክሮች አስቀርቦ ሰምቷል፤ ተከሳሽ ምስክር እንዲያሰሙ ተደጋጋሚ እድል ተሰጥቷቸው ያለበቂ ምክንያት በቀጠሮ ቀንና ሰአት ምስክር ማሰማት አልቻሉም በማለት ምስክር የማሰማት መብታቸውን አልፏል።

በመጨረሻም የቤቱን ማህደር ጨምሮ የግራቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ እንዲሁም ከሳሾች ምስክሮች መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል። በሰጠው ውሳኔ በቀረቡት ማስረጃዎች አከራካሪው ቤት የሟች አቶ ሽፈራው ወ/ኪዳን መሆኑ፤ ሟች ሽፋራው ቤቱን ለሟች ልጃቸው አቶ ጌታቸው ከተከሳሽ ጋር ሳይጋቡ የሰጡ መሆናቸውን አስረድተዋል። ተከሳሽ ቤቱን ከአቶ ጌታቸው ሽፈራው ጋር በትዳር በነበሩበት ጊዜ ያደሱት መሆኑን

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ማስረጃው ያሳያል። በተከሳሽ በኩል የቀረበው የጋብቻ ውል በተመለከተ በወቅቱ ስራ ላይ በነበረው የፍ/ብ/ህ/ቁ 647 እና በተሻሻለው ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 57 መሰረት ተጋቢ ከጋብቻ በፊት በስጦታ ያገኘው የግል ሀብት የግል ሃብቱ ሆኖ የሚቀጥል በመሆኑ በጋብቻ ውሉ ላይ ግንቦት 12 ቀን 1964 ዓ.ም ከአባቴ በውርስ የተሰጠኝን በሙሉ የጋራ ንብረት አድርጌያለሁ በማለት የተጠቀሰው አነጋገር የውርስ ቤቱም ሆነ ንብረቱ የቱ እንደሆነ የማያመለክት እና የውርስ ህግ ድንጋጌዎችን የሚቃረን እንዲሁም የወራሾችን መብት በሚያጣብብ መልኩ የተፃፈ እንጂ ቤቱ የጋራ መሆኑን ለይቶ የሚያመለከት ባለመሆኑ አከራካሪው የቤት ቁጥር 860 የሆነ ቤት የከሳሾች ነው። ስለሆነም ተከሳሽ ለቤቱ እድሳት ያወጡትን ወጪ መጠየቅ መብታቸው ተጠብቆ ለከሳሾች ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል። የኪራይ ጥያቄውን በተመለከተ ተከሳሽ ቤቴ ነው በማለት በትዳር የኖሩበት በመሆኑና ግማሹን ከፍለው ለማከራየታቸው የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ ተከሳሽ የሚከፍሉት የኪራይ ገንዘብ የለም በማለት ወስኗል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሽ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ በቀረበው ማስረጃና የተደረገው ማጣራት ቤቱ የሟች አቶ ሽፈራው ወልደኪዳን የውርስ ሀብት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ፤ ይህን ውርስ ሀብት ሟች አቶ ጌታቸው ሽፈራው በጋብቻ ውል የጋራ ንብረት አድርጌያለሁ ያሉ ቢሆንም በውሉ ቤቱም ሆነ ንብረቱ በትክክል ካለመመልከቱም በላይ የወራሾቹን መብት ሚጋፋ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተመሳሳይ ምክንያት በመስጠት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካቾች በቀን 04/10/2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ቅሬታቸውን ዘርዝረው አቅርበዋል። ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት አቶ ሽፈራው ወልደኪዳን ለሟች ጌታቸው ሽፈራው እና ባለቤታቸው ለሆኑት ወ/ሮ ልኬ አየለ ለጋራ መጠቀሚያነት እንዲሆን ግንቦት 1964 ዓ.ም ተሰጣቸው ስለመሆኑ በጋብቻ ውሉ ላይ ተጠቅሶ እያለ አመልካች ለቤቱ እድሳት ያወጡትን ወጪ የመጠየቅ መብት ተጠብቆ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። ተጠሪዎች ሀምሌ 29/2013 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር አመልካቾች ለቤቱ ያወጡትን የዕድሳት ወጪ የመጠየቅ መብት ተጠብቆ ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ የተሰጠው ውሳኔ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት ለበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቀዋል። አመልካቾችም የመልስ መልስ አቅርበዋል።

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የአያታቸው አቶ ሽፈራው ወ/ኪዳን ንብረት የነበረና እሳቸው ካለፉ በኃላ የአጎታቸው አቶ ጌታቸው ሽፈራው ድርሻ ሁኖ የኖረው የቤት ቁጥር 860 የሆነ ቤት የአመልካቾች አውራሽ አላግባብ ይዘው እያከራዩ እየተጠቀሙበት መሆኑን ጠቅሰው ቤቱን እንዲያስረክቡዋቸውና ኪራይ እንደከፍሏቸው የጠየቁ ሲሆን፤ የአመልካቾች አውራሽ በበኩላቸው ዳኝነት የተጠየቀበት የቤ.ቁ 860 የሆነው ቤት የባለቤቴ አቶ ጌታቸው ሽፈራው እና የእኔ የጋብቻ የጋራ ንብረት ነው፤ ቤቱን ልለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል። የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች አውራሽ ከአቶ ጌታቸው ሽፈራው ጋር በትዳር ለረዥም ዘመን አብረው የኖሩ መሆኑን ተቀብለው በአንጻሩ አመልካች ቤቱ የጋራ ነው በማለት ሚከራከሩበትን የጋብቻ ውል ይዘት መርምረው ውሳኔ ሰጥተዋል። በሰጡት ውሳኔ ግንቦት 12 ቀን 1964 ዓ.ም የተደረገው የጋብቻ ውል ላይ አቶ ጌታቸው ሽፈራው ከአባቴ በውርስ የተሰጠኝን በሙሉ የጋራ የጋብቻ ንብረት አድርጌያለሁ በማለት የጠቀሱት አነጋገር የውርስ ንብረቱ የትኛው እንደሆነ የማያመለክትና ውርስ ህጉን የሚቃረን እንዲሁም የወራሾችን መብት በሚያጣብብ ነው በማለት የጋብቻ ሰነዱን በዚህ ረገድ ተቀባይነት በማሳጣት አከራካሪው የቤት ቁጥር 860 ለተጠሪዎች የሚተላለፍ የውርስ ሀብት ነው፤ አመልካች ሊያስረክቡ ይገባል፤ በሌላም በኩል በጋብቻ ጊዜ ቤቱ ስለታደሰ ለእድሳት ያወጡትን ወጪ አመልካች ይጠይቁ፤ እንዲሁም የኪራይ ጥያቄውን በተመለከተ አመልካች ቤቴ ነው በማለት በትዳር የኖሩበት በመሆኑና ለመከራየቱም ማስረጃ ስለሌለ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስነዋል።

በመሰረቱ በፌዴራሉ የተሻሻለ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 እንዲሁም በፍትሐብሔር ህጉ እንደተመለከተው ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ ያመለክታሉ። በዚህ መልኩ የተገኙ ንብረቶች የግል ሆነው እንዲቀሩ የተለየ ስምምነት በጋብቻ ጊዜ እንዲደረግ ህጉ አያስገድድም። ይህ ማለት ግን ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች እንዲሁም በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የጋራ የጋብቻ ንብረት እንዲሆኑ ስምምነት ሊያደርጉ አይችሉም ማለት አይደለም።

በተያዘው ጉዳይ አቶ ጌታቸው ሽፈራው እና ወ/ሮ ልኬ አየለ ግንቦት 12 ቀን 1964 ዓ.ም የጋብቻ ውል አድርገው በጋብቻ የኖሩ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ተቀብለዋል። በጋብቻ ውሉ ላይ እንደተመለከተው አቶ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ጌታቸው ሽፈራው ወ/ሮ ልኬ አየለን በጋብቻ ሲያገቡ "የቤት እቃ በሙሉ እንዳለና ከአባቴ በውርስ የተሰጠኝ ቤት የግሌ ሳይሆን የጋራ አድርጌ በወር የማገኘውንም ከወጪ ቀሪ ፭፫ ብር ደመወዜን ቆጥሬላት ሳገባት ይህንኑ ገንዘብ በየወሩ አምጥቼ ለእሷ ልሰጥ ወድጃለሁ፤ ለዚህም ውል ውል አባቴ አቶ ተሰማ ኃይሌ ናቸው... "በማለት መስማማታቸው ተመልክቷል። ወ/ሮ ልኬ አየለም በበኩላቸው "አቶ ጌታቸው ሽፈራውን ሳገባ መተዳደሪያ የወር ደመወዝ ብር ፭፫ አድርገውልኛል፤ ከአባታቸው በውርስ ያገኙትን ቤት በሙሉ የጋራ መጠቀሚያ አድርገው ፈርመውልኛል፤ ለዚሁም የውል አባቴ አቶ ፍቅረስላሴ ደጀኔን አድርጌያለሁ .... " በማለት ጋብቻ ፈፅመዋል። በዚህ አግባብ የተቋቋመው ጋብቻ ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ በሞት እስከፈረሰበት ድረስ ፀንቶ የኖረ ሲሆን አከራካሪው የቤት ቁጥር 860 ተጋቢዎች እየኖሩበት መሰረታዊ እድሳትም እየተደረገውበት የጋብቻ ንብረት ሆኖ የኖረ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ካሳለፉት ውሳኔና ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል። አቶ ጌታቸው ሽፈራው እና ወ/ሮ ልኬ አየለ ግንቦት 12 ቀን 1964 ዓ.ም ያደረጉት የጋብቻ ውል ከቤተሰብ ህጉም ሆነ ከውርስ ህጉ አንፃር የሚነቀፍ አልነበረም። መተዳደሪያቸው የሆነው የወር ደመወዝ እና አቶ ጌታቸው በውርስ ያገኙት ቤት የጋራ ሀብትና መኖሪያቸው መሆኑን በመጥቀስ መስማማታቸው ግልጽ ሲሆን ስምምነቱም ህጉን የሚቃረን ነው የሚባልበት ምክንያት የለም።

ይሕ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የጋብቻ ውሉ የውርስ ህጉን የሚቃረን እንዲሁም የወራሾችን መብት በሚያጣብብ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያና ይህን ተከትለው ቤቱ ሙሉ በሙሉ ለተጠሪዎች የሚተላለፍ የአቶ ጌታቸው ሽፈራው የግል ሀብት እንደሆነ ያሳለፉት ውሳኔ ግልፅ ሆኖ ከሚታየው የጋብቻ ስምምነት ቃል እና ከጋብቻው በኋላ ተጋቢዎች ከኖሩበት ሁኔታ የራቀ፤ በጋብቻው በተዋዋዮቹ መካከል የነበረውንና ፀንቶ ለዘመናት ኖረውን የቅንነትና መተማመንን ግንኙነት መሰረት ያላደረገ፤ እንዲሁም በጋብቻ አመሰራረት የኖረውንና ያለውን ልማዳዊ ስርዓት መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል።

በአጠቃላይ በየደረጃው የሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች በቀድሞ አጠራር ወረዳ 04 ቀበሌ 37 በአሁኑ ልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 05/08 የቤ.ቁ 860 የሆነ ቤት በተመለከተ የአሁን አመልካች ግማሽ የጋብቻ ድርሻ የላቸውም በማለት ያሳለፉት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 168292 በቀን 17/08/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 239737 በቀን 06/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ አጠራር ወረዳ 04 ቀበሌ 37 በአሁኑ ልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 05/08 የቤ.ቁ 860 የሆነው ቤት ሟቾች አቶ ጌታቸው ሽፈራው እና ወ/ሮ ልኬ አየለ ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ የጋራ አድርገው ጋብቻው ፀንቶ በኖረበት ጊዜ ሁሉ ተጋቢዎች እየኖሩበት እድሳትም እያደረጉበት የጋብቻ ንብረት ሆኖ የኖረ በመሆኑ የጋራ ሀብታቸው ነው በማለት ወስነናል፡፡ ውርሱም ለወራሾች ሊተላለፍ የሚገባው አቶ ጌታቸው ሽፈራው እና ወ/ሮ ልኬ አየለ በቤቱ ላይ ያላቸው ግማሽ ግማሽ ድርሻ ታሳቢ ተደርጎ ነው ብለናል፡፡

3. ሌላው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

4. በዚህ ፍርድ ቤት ተሰጠው እግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

5. በዚህ ሰበር ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም